# ታሪክ እንደ ሀብል ትውልድ እንደ ሰብል

አብርሃም በየነ

ኢሕአፓ ባገር ቤት ሰሞነተኛ ርዕስ ሆኖ መሰንበቱን የሚያንፀባርቁ ሁለት መጣጥፎች ደረሱኝ። ሁለቱም የመፅሐፍ ዳሰሳዎች ነበሩ። አንደኛው በተመስገን ደሳለኝ፤ **"ኢሕአፓና የገሃነም ቅፅሩ"** የሚል ሲሆን፤ ሌላኛው ደግሞ በብርሃኑ ደቦጭ (የታሪክ ተመራማሪ)፤ **"የኢሕአፓዊነት ስነልቦናን ከማከም ዕርም ማውጣት"** የሚል ነው። የቀዳማዩ ርዕስ ትኩረት የህይዎት ተፈራው Tower in the Sky እና የክፍሉ ታደሰው ያ ትውልድ ሲሆኑ የካልአዩ ዳሰሳ ደግሞ በቆንጅት ብርሃን ምርኮኛ፤ በህይዎት ተፈራ Tower in the Sky እና በካህሳይ አብርሃ የአሲምባ ፍቅር ዙሪያ ዳሰሳውን ያሽከረክራል ። ሁለቱም ሀምሌ 2005 ዓ. ም. በወጣው ፋክት መፅሔት ቅፅ2 ቁጥር 5 ነበር ለንባብ የበቁት።

የተመስገኑ ዳሰሳ በይቀጥላል እንደ ተንጠለጠለ ነው። የብርሃኑ "ሳይኮ አናሊሲስ" ግን ደራሲዎቹን ቡታ ሰዳጅ ድርሳኖቻቸውንም ዕርም አስዎጭ ገፅታ ሰጥቶ ተቋጭቷል። እኔም በብርሃኑው ዳሰሳ ዙሪያ ውይይት ቢከፈት ጉዳት አይኖረውም ከሚል እሳቤ ተነስቸ ብዕርና ወረቀት አገናኘሁ። ዳሰሳው ቀደምቱን ትውልድ ራሱን የማይተካ መኻን ትውልድ ፤ ታሪኩንም ከራሱ ሞት ጋር ወደ መቃብር ይዞ የሚያወርድና ለተተኪው ትውልድ ትውፊት ጥሎ የማያልፍ አሸራ አልቦ ኩነት ሆኖ የተሳለ መሰለኝ። እናም ታሪክ ምንድን ነው? ስነልቦናስ? የሚሉ ጥያቄዎችን አጫሩብኝ።

ታሪክ የቀደምቱ ትውልድ ኩነቶች አሸራ ነው። የሰዎች ትግብርት ክንውን እንደመሆኑ ከድክመቶቹ እና ከጥንካሬዎቹ መለበሚያና ተመክሮ ይገበይበት ዘንድም ታሪክ የሚፃፍ መሰለኝ። ታሪክ ተወራሽ ትውፊት እንጂ የሰነልቦና የኑዛዜ ቃል ተደርጎ መውሰዱ የግንዛቤ ችግር መሰለኝ ። የተዳሰሱት መጻህፍትም ተተኪውን ትውልድ ዕርም እያስወጡ ተስፋ የሚይስቆርጡና ቀዳሚውንም ትውልድ ወደ መቃብር የሚሸኙ የሙሾ ስንኞች ተደርገው መወሰዳቸው እንደምታ ያለው ይመስላል። ሰነልቦናም እንዲሁ ከፈጣሪው ጋር ወደ መቃብር የሚወርድ ክስተት ሆኖ መታየቱ ታሪክን ከሃዲዱ ያሰወጣዋል።

1. *"ስለአብዮቱ ዘመን በሚነገርባቸው ኢጋጣሚዎች ኢህኢፓዊነት የምራል ገናናነት እንዳለበት ታዝቤአለሁ። ይህ ስነልቦና ድርጅቱ ብዙዎችን ለማንቀሳቀስ ስለመቻሉ በነመኢሶን ኢድርባይነት፤ በደርግ የመሳሪያ ባለቤትነት ባይጨፈጨፍ ኢትዮጵያን ኢዳኝ ተደርጎ የማሰብ ዝንባሌ እንዳለበት የሚያሳይ ነው። ይህንን ነው የኢህኢፓዊነት ስነልቦና የምለው። "(ገፅ 9)*

*2." ሶስቱም በየበኩላቸው በሰሩት ሥራ ዕርማቸውን እንዳወጡ ሊቆጠር ይችላል። ይህ አቀራረብ ከእስካሁኑ የኢህኢፓዊነት ስነልቦናን ማከም ተላቆ ለስነልቦናው ግብአተ- መሬትን በማመቻቸት ራስን ከዕውነታ ጋር የማስታረቅና ለአዲስ ከባቢና ስነልቦና የመዘጋጃ/ የማዘጋጃ በጎ ጅምር ተደርጎ የሚወሰድ ነው። ይህም በተወሰደው ግዙፍ መስዋዕትነት መንስኤነት የተፈጠረው የኢህኢፓዊነት ስነልቦና ያዛባውን የኢህ ኢፓ ታሪክ ነፃ ለማውጣት ደፋር የሚሰኝ ዘመነኛ እርምጃ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል።" ( ገፅ 28)*

*3. እንግዲህ ከዚህ አኳያ ስናያቸው ነው የዛሬዎቹ ሶስት መፃህፍት የኢህኢፓን ሰነልቦና ከማስተዛዘን ወይም ደግሞ ለምጠገን ከመሞከር የስነልቦናው ግብአተ መሬት ላይ የሚነበብ የሕይዎት ታሪክ በማቅረብ ዕርም ማውጣትን በአፍ ሳያውጁ እንደመረጡ የምንረዳው። (ገፅ 28)*

*“. . . . . . በነመኢሶን አደርባይነት፤ በደርግ የመሳሪያ ባለቤትነት ባይጨፈጨፍ ኢትዮጵያን አዳኝ ተደርጎ የማሰብ ዝንባሌ እንዳለበት የሚያሳይ ነው። ይህንን ነው የኢህአፓዊነት ስነልቦና የምለው” የሚለን በርሃኑ ፀፀት ወይም ቁጭት ነው። ፀፀት/ቁጭት የሚረሳ ስሜት ስለሆነ የመዳበርና የመትግበር ዘላቂ ባህሪያት የሉትም። ፀፀት ዘመን አይሻገርም።ስነልቦና ግን የሚዳበርና የሚተገበር ክስተት ከመሆኑም በላይ ከትልድ ወደ ትውልድ የመተላለፍ ዘላቂ ባህሪይ የተላበሰ ጽንሰ ሀሳብ ነው። “. . . . .ይህንን ነው የኢህአፓዊነት ስነልቦና የምለው” የሚለን በርሃኑ ፀፀት እንጂ ስነልቦና አይደለም። ብርሃኑ የኢህአፓዊነት ስነልቦና የሚለው ፀፀት ትውልዱ ሲከስም አብሮ ይከስማል።*

*የኢህ አፓዊነት ስነልቦና መነሻው ኢህአፓ ይሁን እንጂ ስነልቦናው ግን ከድርጅቱ ህልውና ጋር እስከ መቃብር አይጓዝም። ፈጣሪው አካል ለፈጠረው ስነልቦና መተግበር እንደ ኢህአፓ ህይወቱን ጨምሮ ብዙ ዋጋ ሊከፍል ይችላል። በዚህ መልክ አይዛክ ኒውተን ፤ ኮፐርኒከስ፤ አንስታይንና ሌሎቹም ሳይንቲስቶች በፈጠሯቸው ስነልቦናዎች ሳቢያ ከሮማው ጳጳስ ብዙ ፈተና ተቀብለዋል። ብዞዎቹም ሞት የተፈረደባቸው ነበሩ። ሳይንቲስቶቹ ዛሬ በህይወት የሉም ። የፈጠሯቸው ስነልቦናዎች ግን ከነርሱ ህልፈት በኋላ ዛሬም ድረስ ህያው ናቸው። የኢህአፓዊነት ስነልቦናም ከደርጅቱ መጥፋት ጋር አብሮ አይጠፋም። ለምን ቢሉ የአንድ ስነልቦና መባቀያ አፈረ-መሬቱ ህዝብ ነው። የኢህአፓዊነት ስነልቦና መባቀያ አፈረ-መሬቱ የፍትህ መጓደል፤ የየጾታ፤ የሃይማኖት፤ የመደብና የብሄር ዕኩልነት አለመኖር፤ የመሬት ላራሹ ጥያቄ፤ የዴሞክራሲ ጥያቄ ፤ የሰብአዊ መብቶች አለመከበር ጥያቄና ሕዝብ የስልጣኑ ባለቤት አለመሆን ነበሩ። ኢህአፓም ለነዚህ ሕዝባዊ ጥያቄዎች የማያወላዳ መልስ ማግኘት የሚቻለው በፓርቲ ተደራጅቶ ትግሉ የሚጠይቀውን ማናቸውንም መስዋዕትነት እየከፈሉ መታገል እንደሆነ አምኖ ትግሉን ጀመረ። እናም ተደራጅቶ በቆራጥነት መታገልን ለኢትዮጵያ ህዝብ አስተዋወቀ። ይህ ነው የኢህአፓዊነት ስነልቦና ሊባል የሚችለው።*

*ዓለማችን የብዙ ስነልቦናዎች ውጤት ነች። ካርል ማርክስ በዘመኑ የፈጠረው ስነልቦና ማርክሲዝም ዓለምን በሁለት ጎራ አቁሞ ጠመንጃ አማዟል። ደም አቃብቷል። ማርክስ ከሞተ ዘመናት ተቆጥረዋል። ስነልቦናው ግን ህያው ነው። መኖር የቻለ ይኖራልንና (survival of the fittest ) አዝጋሚ ለውጥን (evolution )ፈጥሮ ያለፈው ዳርዊን ዛሬ በህይወት የለም። ስነልቦናው ግን ዛሬም ድረስ በክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች ጥላወጊ ተደርጎ መታየቱ እንደቀጠለ ነው።* የናዚዎች ስነልቦናም ከነሂትለር ጋር አብሮ አልሞተም። ዛሬም ድረስ በብዙ ጀርመኖች ይተገበራል። ይልቁንም አልፎ ተርፎ ከጀርመን ውጭ በተለያዩ ሀገራት አሜሪካን ጨምሮ በኒዎ ናዚዎች ህልውናውን ጠብቆ እየኖረ ነው። የዛሬይቱ እስራኤልም ሁለት ሺህ ዘመን ያስቆጠረ የጺዎናዊነት ስነልቦና ውጤት ነች።

በዘመነ መሳፍንት መገባደጃ የተነሱት አጼ ቴወድሮስ የጀመሩት(የፈጠሩት) ኢትዮጵያን አንድ የማድረግ ስነልቦና መቅደላ ላይ ከቴወድሮስ ጋር አብሮ አልተቀበረም። ስነልቦናው በአጼ ዮሐንስ ቀጥሎም በአጼ ሚኒሊክ ዳብሮ ዛሬ ድረስ ደርሷል። ባንጻሩም ኢጣሊያና እንግሊዝ ኤርትራን ለቅቀው ሲወጡና ከወጡም በኋላ ኢትዮጵያን የመቆራረስ ስነልቦና ፈጥረው ነበር። ሰሜኑን የትግራይ-ትግርኚ፤ መሃሉን የአማራ ፤ ደቡቡን ደግም የኦረሞ ትንንሽ መንግስቶች የመቆርቆር እቅድ ነበራቸው። ይህም ስነልቦና ከቅኝ አገዛዝ ሥርዓት ጋር ግብዓተ መሬቱ አልተከናወነም። ይልቁንም በሸዐቢያ፤ በወያኔና በኦነግ ሊተገበር እድሜ ሸምቶ ይኸው እያፋጀን ይገኛል።

የትም ይሁን የት ስነልቦናዎችን የፈጠሩ አካሎች ስነልቦናዎቻቸው ሲተገበሩ ለማየት በህይወት መኖር አላስፈለጋቸውም። ኢሕአፓም የኢሕአፓዊነትን ሰነልቦና እስከ መጨረሻው ሲተገበር ለማየት እንደ ድርጅት መቆየት አያስፈልገውም። የአንድን ስነልቦና መነሻና መዳረሻ (ውልደትና ሞት) የሚውስኑት ለስነልቦናው መባቀያ አፈረ-መሬት የነበሩት ክስተቶች በህብረተሰቡ ውስጥ ህልው መሆንና አለመሆን ስለሆነ የተጠቀሱት ደራሲያንም ከድርጅቱ ራሳቸውን ስላገለሉ የኢሕአፓዊነትን ስነልቦና

ግብአ- ተመሬት አያረጋግጡም። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ታሪክም የኑዛዜ ቃል ተደርጎ መወሰዱ እንደ ስነልቦናው ግንዛቤ ህፀፅ አለው። ብርሃኑ ግን ደራሲያኑ ያላለሙትን አሳልሞ ለግል ዕምነቱ መናኛ ሊያደርጋቸው ሞክሯል።

ታሪክ የአብዮተኞች ችቦ የቅብብሎሽ ውጤት ነው። የአብዮቱ ፋና ወጊ ቡድን ሲወድቅ ችቦው በሌላ አብዮታዊ ቡድን ተይዞ ይቀጥላል። የነግርማሜን የለውጥ ችቦ ያ ትውልድ ከአስራ አራት ዓመታት በኋላ እንዳነሳው የኢህአፓንም ችቦ ሌላ ቀጣይ አብዮታዊ ቡድን/ትውልድ አንድ ቀን ያነሳዋል። ነገሩ የጊዜ ጉዳይ እንጂ ከስተቱ አይቀሬ ነው። ብርሃኑ ደቦጭ እንደሚያስበው ሳይሆን ትግሉ ተዳፈነ እንጂ አልሞተም። አመፁን ያዳፈኑት አስገዳጅ ሁኔታዎችም የማቱሳላን ዕድሜ እንደማያገኙ ከታሪክ ይማሯል። በነገራችን ላይ የሰው ልጅ ብባህሪው የታሪክ ፍራሽ አዳሽ ስለሆነ ታሪክም እራሷን ስትደግም ኖራለች።

ይመስለናል እንጂ ሁሉም ነገር ህልፊት

ተመልሶ መጭ ነው ያለፈው ወደ ፊት፤

ትናንት ይመስለናል በሽኚት ተጉዟል

ግን መልሶ መጭ ነው የነገን ቁልፍ ይዟል፤ እንዲሉ የትናንቱ አብዮት በዛሬው የግፍ አገዛዝ ማህፀን ውስጥ ተረግዟል።

ሐምሌ 1 ቀን 2005 ዓ.ም. በተደረገው የ “tower in the sky” መፅሐፍ ውይይት ለመናገር እስኪያቅታቸው ሲቃ የተናነቃቸው ወገኖቼና ከመድረኩ በስሜት በዘመኑ የነበሩትን ልዩና ምጡቅ አድርገው ለማቅረብ የሞከሩት ምሁር ለስነልቦናው ቀጣይነት ጥሩ ማሳያ ናቸው። መቼም በ20ና 30 ዓመት ዕድሜአቸው ለሰሩት ሥራ ዛሬም በጭፍን መከራከራቸው እነዚህ የወደቁ እኩዮቻቸውን እያሰቡ መሆኑ ቢሰማኝም ዛሬም ለሰማዕታቱ ታማኝ ሊሆኑ የሚችሉት በዚህ ዓይነት ስለመሆኑ ማመናቸው ግን ትዝብት ላይ እንደሚጥላቸውና ከስነልቦናው ለመላቀቅ ብዙ እንደሚቀራቸው መጠቆም እፈልጋለሁ።

እንደ ፍየል ቅጠል እያመነዠኩ ብዕርን በወረቀት ጫንቃ ላይ ማስለቀስ ላይቸግር ይችላል። ወፌ ይላላ ተመዝኖ/ተሰቅሎ በመኢሶንና በሰደድ ቅልብ ካድሬ ቅብብሎሽ የሚወርደውን የስየል (torture) ዓይነት ተቋቁሞ ምስጢር ሳያዘልቁ የጓዶቹን ህይዎት ማትረፍ ግን ሃሞት ይጠይቃል። መሆንና መናገር ሁለት የተለያዩ ነገሮች ናቸው። እንደ አርስጣጢለስ እየተናገሩ እንደ ቄሳር መኖር ቀላል ነው፤ እንደ ሶቅራጥስ የተናገሩትን ሆኖ መኖር ግን በእጅጉ ይከብዳል እንዲሉ ብርሃኑ ኢህአፓዎችን መሆን አይቻለውም። ለወደፊቱም እንዲሆን አይጠበቅበትም።

የደርግን ዕስርቤቶች በራፍ ዕረግጦ የማያውቀው ብርሃኑ ለመናገር ሲቃ በተናነቃቸው ኢህአፓዎች ሲሳለቅ “ . . . ለሰማዕታቱ ታማኝ ሊሆኑ የሚችሉት በዚህ ዓይነት ስለመሆኑ ማመናቸው ግን ትዝብት ላይ እንደሚጥላቸውና ከስነልቦናው ለመላቀቅ ብዙ እንደሚቀራቸው መጠቆም እፈልጋለሁ” ሲለን የሞራል ገናናነት ያለው ይመስላል። ሀቁ ግን ባዶ መከፈስ ነው። የብርሃኑ ደቦጭ ስላቃዊ አገላለፅ ከጀርባው ቁስል ያለው ይመስላል። የኢህአፓ መልሶ የመጠናከር ሙከራ ብርሃኑን የህሊና ዕረፍት የነፈገው ይመስላል። ለዚህ አባባሌ ያለኝ አመክንዮ በገጽ28 “የኢህአፓዊነት ስነልቦናን ማከም ተላቆ ለስንልቦናው ግብዓተ መሬትን ማመቻቸት ራስን ከዕውነታ ጋር የማስታረቅና ለአዲስ ከባቢና ስነልቦና

የመዘጋጃ/የማዘጋጃ በጎ ጅምር ተደርጎ የሚወሰድ ነው፤ የሚለው አገላለጹ ነው። ብርሃኑ የሚሳለቀው የተኮላሸ ወኔውን ለማባበል ከሆነ ነገሩ ቂም የለውም። ለምን ቢባል ሰው በምክኒያት ይኖራልና።

ተቀምጨዎች (do-nothings) የመኮፈስ ባህሪያቸውን ተከናንበው በህዝብ ፊት ጥሩ ሰው ለመምሰል፤ ለህብረተሰቡም አሳቢና ተራዳኢ መስሎ ለመታየት፤ የስብዕና ክብር ሊጎናፀፉ ይዳዳቸዋል። በተግባር ሲታዩ ግን እንደ ብርሃኑ ደቦጭ ከመሆን ያለፈ ስብዕና የላቸውም። ተቀምጨዎች በህብረተሰቡ ማህበራዊ ለውጥ ራሳቸውን እያቀሰሱ ነገር ግን ስለፍትህ፤ ስለ ዕኩልነት፤ ወዘተ በሚደረጉት ትግሎች ራሳቸውን ያገላሉ። ሌሎች የሚወስዷቸውን እርምጃዎች ያጣጥላሉ። በግብዓታችሁ እስማማለሁ ለዚያ ግብዓት ስኬታማነት በምትወስዱት እርምጃ ግን አልስማማም የሚለው ታፔላቸው ነው የተቀምጨዎች መታወቂያ የሚል አገላለፅ አንድ ቦታ ላይ ማንበቤን አስታውሳለሁ።

*“ያ ትውልድ የተባለው ያለመቻቻል ምልክት ነው የሚሉ ያዲሱ ትውልድ አባላት ነቀፌታን እና ኢህአፓዊያኑ “ያ ትውልድ” የሚል ስም ለራሳቸው ሰጥተው ሁሉንም የአብዮቱን ዘመን ገድል ጠቅለለው የመውሰድ ዝንባሌ አሳይተዋል የሚሉ ወቀሳዎች ናቸው።”* (ገፅ 28)

“ ኢህአፓዊያኑ ‘ያ ትውልድ’ የሚል ስም ለራሳቸው ሰጥተው ሁሉንም የአብዮቱን ዘመን ገድል ጠቅልለው የመውሰድ ዝንባሌ አሳይተውል”፤ የምትለዋ ወቀሳ ውሃ አትቋጥርም። በደርግ ዙሪያ በነበሩት ቡድኖች ውስጥ የመኢሶን፤ የወዝሊግ፤ የሰደድ፤ የኢጭአትና የማሊሬድአባላት ከአብዮቱ በፊት በየግላቸው ተሳትፎ ያበረከቱት አስተዋጾኦ ሊኖራቸው ይችላል። አብዮቱ ከፈነዳ በኋላ ግን ታሪካቸው የሚያኮራ ሳይሆን የሚያሳፍር ነበር። ሁሉም ቡድኖች በደርግ ብብት ስር ተወሽቀው የደርግ መሳሪያ ከመሆን ያለፈ በኢህአፓ ሊወሰድባቸው የሚችል አብዮታዊ ገድል አልነበራቸውም። እንዳውም ተሳትፏቸው በቀጥታም ይሁን በተዛዋሪ በንጹሃን ደም እጃቸውን ስለአወየበው ታሪካቸው ወንጀለኛ ያደርጋቸዋል። “ ያ ትውልድ የተባለው ያለመቻቻል ምልክት ነው የሚሉ. . . ያዲሱ ትውልድ ነቀፌታም” ተጠቅሷል። ይህንን ነቀፌታ እንዲህ ከፋፍሎ መመልከቱ ለግንዛቤ ይረዳል።

## ያ ትውልድ

ያ ትውልድና ይህ ትውልድ የነበሩባቸው/ያሉባቸው ዘመኖች የየራሳቸውን ተፅዕኖ በየትውልዶቹ ላይ ጭነዋል። በያ ትውልድ ዘመን በርካታ የአፍሪቃ አገሮች በቅኝ አገዛዝ ቀንበር ስር ነበሩ። እነዚህ አፍሪቃዊያን ወንድሞቻችን ከምእራቡ ቅኝ አገዛዝ ቀንበር ለመላቀቅ የሚያደርጉትን ተጋድሎ ያ ትውልድ የመደገፍ የሞራል ግዴታ ነበረበት። ስለሆነም የቅኝ አገዛዙ አውራ ከነበረችው አሜሪካ ጋር ሽርካ የነበረውን የአፄውን አገዛዝም በተዛማጅ መቃወም ነበረበት። እናም ፊቱን ወደ ምስራቅ እንዲያዞር ሁኔታው አስገድዶታል። ከቅኝ አገዛዝ ቀንበር ለመላቀቅ ይታገሉ ለነበሩት አንጎላ፤ ሞዛምቢክ፤ ናሚቢያ፤ አልጀሪያና ደቡብ አፍሪቃ የቬትናም ጦርነት የራሱ የሆነ የምኩራብነት ባህሪይ ነበረው። በዚሁ ላይ የቼ ጉቬራ ፀረ-ኢምፔሪያሊስት ተግልና የኩባ ነፃነት የበኩሉን ስነልቦናዊ ተፅዕኖ አሳድሯል። እነዚህ ዓለም አቀፍ ሁኔታዎች የምዕራቡን ዓለም ሰማይ አጥቁረው የምስራቁን ግን ስላቀሉት ያ ትውልድም እንደ ምስራቁ ሰማይ ቀላ። እናም እንደ ሆቺሚንህ........ እንደ ቼ ጉቬራ. . . ብሎ ዘመረ።

ያ ትውልድ ከቀደምቱ ትውልድ የወረሰው የስልጣን አወራረስ ባህል የሃይል ባህል ነው። በቀደምቱ ታሪካችን ስልጣን ከነገስታት ወደ ነገስታት ይሸጋገር የነበረው በጠመንጃ አፈሙዝ እንጂ በምርጫ ሳጥን አልነበረም። የፖለቲካ ልዩነትም በቀደምቱ ትውልዶች ባህል ዕልባት ያገኝ የነበረው በሃይል እንጂ በሰከነ የጠረጴዛ ዙሪያ ውይይት አልነበረም። ይልቁንም ሃይል የስልጣን ባለቤት እንደሚያደርግ ነው ያ ትውልድ የወረሰው ባህል። እናም ሌላ ምርጫ ያልነበረው ትውልድ

የነበረውን ብቸኛ አማራጭ እንዲጠቀም ሁኔታው አስገድዶታል። በዚሁ ላይ ደግሞ የፊውዳል ትምክህት በወጣትነት ትኩሳት ላይ ታክሎ ሁሉም ነገር ባሩድ ባሩድ ሸተተ።

ያ ትውልድ ይኖርበት የነበረው ዘመን እንደዛሬው ዓለምን ከጣቱ ጫፍ (finger tips) የሚያይበት ጉጉል፤ ፌስ ቡክ፤ ወይም አልጀዚራና ሲኤንኤን አልነበረውም። ብቸኛዋ የመገናኛ መሳሪያው የትራንዚስተር ሬዲዮ ነበረች። ስለሆነም ከዲሞክራሲ ባህል ጋር የነበረው ትውውቅ ውሱን እጅግ በጣም ውሱን ስለነበር የመቻቻል ባህሪይ አይጠበቅበትም። በዚህ ሁሉ ላይ ደግሞ የመደብ ትግል ሲጨመርበት ውጤቱ አስከፊ ሊሆን ችሏል። የኢህአፓ ሁኔታ ደግሞ ከመኢሶን፤ ከኢጭአት፤ ከወዝ ሊግና ከማሊሬድ የተለየ ነበር። እነዚህ ቡድኖች በሙሉ በደርግ ጉያ ስር የነበሩ ሲሆን ኢህአፓ ግን ከነዚህ ቡድኖች በተጨማሪ ሰው ለመግደል ከሰለጠነ አውሬ (ወታደር) ጋር ነበር ፊት ለፊት የተፋጠጠው።

## ይህ ትውልድ

ይህኛው ትውልድ ከርሱ በፊት እንደነበረው ያ ትውልድ ምኩራብ የሚሆነው ትውልድ ለማግኘት አልታደለም። ምኩራብ ሊሆነው ይችል የነበረው ያ ትውልድ በቀይ ሽበር ስላለቀ የትውልድ ክፍተት ተፈጥሯል። ቀይ ሽብር በፈጠረው የፍርሃት ቆፈን ላይ ከቋት በታች የሆነው የወያኔ ድህነት ታክሎበት ይህን ትውልድ አንገቱን እንዲደፋ አስገድዶታል። እናም ይህኛው ትውልድ የሚታገለው እንዳለፈው ትውልድ ትከሻው ላይ የተጫነውን የጭቆና ቀንበር ሳይሆን እንቅልፍ ነፍጎት የሚይድረውን የሆዱን ትል እንዲሆን ሁኔታው አስገድዶታል።

ይህኛው ትውልድ ግሎቫላይዜሽን በፈጠረው አሉታዊም ሆነ አወንታዊ ተፅዕኖ እኔነቱን አጥቷል። እናም በደረሰበት የባህል መሸርሸር ሳቢያ እሱነቱን በውል እንዳይገነዘብ ሆኗል። ክብሩን አጥቶ ተዋርዶና ተረግጦ እንዲኖር ዓለማቀፋዊና ሀገር አቀፋዊ ሆኔታዎች ተባብረውበታል። ሰለሆነም ሁለቱ ትውልዶች እንዲህ ይለያያሉ፡-

ያ ትውልድ ሲከፋው

እንደ ሆቺሚንህ እንደ ቼ ጉቬራ

በዱር በገደሉ ፋኖ ተሰማራ ብሎ በመዘመር ወይ በርሃ ይገባል ወይ በጎዳና ይተማል።

ይህኛው ትውልድ ግን ሲከፋው

ከፍየሎች ላንዱ እንደ እኔ ለከፋው

የሆዴን ባጫውተው ያፉን ቅጠል ተፋው ብሎ ወደ ቅጠል ሽምጠጣው ይሰማራል። እናም ወቀሳውም ሆነ ሙገሳው ከነዚህ ያለፉና የአሁን ጭብጦች አኳያ እየታየ ቢሆን ታሪክም እንደ ሀብል ይወረሳል። ትውልድም እንደ ሰብል ፍሬው ይሰበሰባል።

ነሃሴ 2005

aderaj3106@gmail.com